# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 6 ቁጥር 3 ሚያዝያ 21 ቀን 2011 ዓ.ም.

## የሜይ ዴይ ሰማዕታት 42ኛ ዓመት መዘክርታ

*(የሜይ ዴይ ሰማዕታት 42ኛ ዓመት እና የ«ያ ትውልድ ተቋም» ድረ ገጽ 7ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ)*

መለስ ብለን ስናስታውስ ለምን? ምን ዓይነት የጭካኔ ዘመን? እውን የሰው ልጅ በራሱ ዜጋ ያውም በታዳጊ ሕፃናትና ወጣቶች እንዲህ ይጨክናል? ቢያስብልም ሆኗል፤ ተደርጓል። በኢትዮጵያዊነት ባህላችን ሰው ሲሞት አስከሬን ከተገኘ እንደ እምነታችን የቀብር ሥነ ሥርዓት ይከናወናል። ቤተሰብ፣ ወዳጅ፣ ዘመድ በልቅሶ የመጨረሻውን ግብዓተ መሬት በመፈጸም እርማቸውን ያወጣሉ። መርዶም ከሆነ እንደ ባህላችን ቤተሰቡን ዘመድ፣ ወዳጅ በማርዳት ያስተዛዝናሉ፣ ያጽናናሉ። ይህ ኢትዮጵያዊ ኩሩ ባህላችን ነው። በጦርነት ወቅት የሟችን አስከሬን ለቤተሰብ መስጠት አዳጋችና አመቺ ባለመሆኑ ነው "የወንድ ልጅ እናት ታጠቂ በገመድ ልጅሽን አሞራ እንጂ አይቀብረውም ዘመድ" ተብሎ የተዜመው። አዎ! በተለያየ የሀገር ዳር ድንበርን የማስከበር ጦርነቶችም ሆነ የእርስ በርስ ግጭቶች በጫካ በዱሩ የቀሩ ወገኖች በጅምላ ይዘከራሉ፣ ይወሳሉ። ታሪካቸው፣ ተጋድሏቸው ይፃፋል፣ ይተረካል ለትውልድ ይተላለፋል። የጦርነቱን ቦታ በመጥቀስ ዐድዋ፣ ደጓሌ፣ መተማ፣ መቅደላ፣ ማይጨው፣ ሌላም ሌላ ወይም ከቀናት በማዛመድ የካቲት 12 ሰማዕታት፣ "የታህሳስ ግርግር" እየተባለ ሟቾች ይነሳሉ ወቅቱ ይዘከራል፣ ታሪኩ በተቻለ ሳይዛባ ለትውልድ ይተላለፋል።

በኢትዮጵያ አገዛዞች ታሪክ ቤተሰብ፣ ዘመድ አዝማድ፣ ወዳጅ መርዶ በሬድዮ የሰማበት የመጀመሪያው አስከፊ ቀን ኅዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም. ነበር። ቤተሰብ የሟችን አስከሬን አግኝቶ መቅበር አይደለም ማልቀስ የተከለከለበት ዘመን። ደርግ 60ዎቹን ገድሎ የፈጸመው አጸያፊ ተግባር። "በአገዛዝ ዘመናቸው በአደረጉት ጥፋት እርምጃ ስለተወሰደባቸው አስከሬን በመረከብ እርማችሁን አውጡ" የማለት ኢትዮጵያዊ ከበሬታ ያልነበረው ፍጅት። በቀጣይነት ቦታው እንኳ ሳይታወቅ ተለመደና ደርግ ገደለ እራሱ ቀበረ። ለዚህም ነው "የወጣቶች እናት ታጠቂ በገመድ ልጅሽን ደርግ እንጂ አይቀብረውም ዘመድ" የተባለበት ዘመኑ ሲያል።

በዚህ ሂደት የቀጠለው የደርግ ግድያ የዛሬ 42 ዓመት ዓርብ ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. ይወስደናል። በመላ ኢትዮጵያ በሺዎች የሚቆጠሩ ሕፃናት፣ ታዳጊ ሕፃናትና ወጣቶች በደርግ ቢ አር የተጨፈጨፉበት ቀን፣ ወላጅ ዘመድ የልጆቹን አስከሬን ያላገኙበት፣ ያልቀበሩበት የዋይታና የጩኸት ዘመን። ይህንን ወቅት ስናስታውስ በአዲስ አበባ ብቻ ከ2 ሺህ የማያንሱ ወጣቶች በአንድ ምሽት በደርግ ገዳዮች እምሽክ ብለዋል። ከአንድ ቤት እስከ አራት ወንድማማቾች የተገደሉበት ዘመን። አንድም ቤተሰብ እንደ ባህሉ አልቅሶ አልቀበራቸውም፣ ሐውልት አላቆመላቸውም። ከስድስት ዓመት ተኩል በፊት በተቋም ደረጃ የተመሠረተው "ያ ትውልድ ተቋም" ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ

ለሚዘክራቸው የሜይ ዴይ ሰማዕታት ክብር ለናንተ ብለን ጊዜ ባያድለንም በህሊናችን ሰንደቅ ዓላማችንን ዝቅ አድርገንላችኋል፣ አንገታችንን ደፋ በማድረግ ፀሎታችንን በህሊናችን አድርገናል። ታሪካችሁ ህያው ነው! እንላችኋለን።

የዛሬ 42 ዓመት አርብ ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. በመላዋ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ዓለም አቀፍ የሠራተኞችን ቀን፡ ሜይ ዴይ ምክንያት በማድረግ አባላቱና ደጋፊዎቹ በየአካባቢያቸው በሰላማዊ ሰልፍ የተነሱበትን ዓላማ በማስተጋባት ለላብ አደሩ የትግል አንድነታቸውን ለመግለጽ ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት ጀምሮ ለሰላማዊ ሰልፍ ተንቀሳቀሱ።

ደርግ የደርጉ ሊቀ መንበር የነበሩትን ብ/ጄ ተፈሪ በንቴን ጨምሮ ሰባት የደርግ አባላትን ጥር 26 ቀን 1969 ዓ.ም. በፋሽስቱ መንግሥቱ ኃይለማርያም አቀነባባሪነት ከረሸነ በኋላ የአብዮቱን አጥቂነት ለማጉላት ሚያዝያ 6 ቀን 1969 ዓ.ም. ከሚጠጣው ደም አንደኛው የኢሕአፓ ልጆችን ለመሆኑ በአብዮት አደባባይ ደም የተሞላ ጠርሙስ ከመሬት በመከስከስ ገዳይነቱን አወጀ። በቀጣይነት የቀይ ሽብር ድህረ ዝግጅት "ነፃ እርምጃ" በየአካባቢው በደርግ ካድሬዎች ተጀመረ። ድርጊቱ ኢሕአፓ ተሆነ አልተሆነ ሳይሆን ወጣት የተባለን በድንገት መጥቶ በመረሸን ሌሎችን ማሸበርና ማስደንገጥ ግቡ ነበር። ይህ ወቅት የበርካታዎችን ሕይወት በየደቂቃው እየነጠቀ ያለቀባሪ ያስቀረበት ፋሽስታዊ ዘመን ነበር።

ዓለም አቀፍ የላብ አደሩን ቀን ሜይ ዴይ 1969 ዓ.ም. ከደርግ ልቅ ያጣ ጭፍጨፋ አንፃር በዕለቱ ማክበር እንደማይቻል የተገነዘበው ኢሕአፓ፡ ሁለት ቀናት ቀደም ብሎ ለኢትዮጵያ ሀገሩና ለጭቁን ሕዝብ ያለውን ታማኝነት፣ የዓላማ ጽናትና ቆራጥነት ለማረጋገጥ የተዘጋጀው የሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. ሰልፍ ከድርጅቱ እየከዱ ወደ ደርግ መግባት በጀመሩ አንጃዎች ሙሉ መረጃ ለደርግ በመድረሱ መንግሥቱ ኃ/ማርያምና ጀሌዎቹ አብዮት አደባባይ በምሳሌነት ያፈሰሱትን ደም ሊጠጡ ቋምጠውና አድፍጠው ተጠባበቁ።

በአብዛኛው አካባቢዎች ሰልፉ ሲጀመርና የጥይት ሩምታ ሲለቀቅ እኩል ሆነ። በርካታ ሕፃናትና ወጣቶች "ፍጹም ነው እምነቴ" እንዳሉ ሕይወታቸውን ለትግሉ ሰጡ። አዲስ አበባ ያንዥበበባት የደም ደመና አጥለቀለቃት። አስፋልቶች በወጣቶች ደም ታጠቡ። የላብ አደሩ ድምጽ ደም። በየአካባቢው ምሽቱ ደም በጠማቸው የደርግ ገዳዮች ሽብር ሆነ። ማ ይሙት ማ ይትረፍ መለየት እስኪያቅት ተኩስና ለቅሶ ለሊቱን አድረውበት፡ ለተረኛው ንጋት ለቀቁ። ነጠላዎች ተዘቀዘቁ፡ ቀሚሶች ጥቁር ሆኑ፡ እናቶች አባቶች ሀዘን፡ ቁጭትና እየዬ ዋጣቸው። ልክ የዛሬ 42 ዓመት።

አብረን ተሰልፈን፡ አብረን ጮኸን፡ አብረን ታግለን፡ አብረን ተሰቃይተን በተለያየ አጋጣሚ ዛሬ በሕይወት ያለን የዚያ ትውልድ አባላት ቢያንስ ልንዘክራቸው፡ ልናስባቸው ይገባል። ደማቸውን ያፈሰሱ አጥንታቸውን የከሰከሱት "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም" "የዴሞክራሲ መብት ያለገደብ ለሁሉም" እየፈከሩ፡ "ደህ ደህ ምን ታየበት፤ እንዳይማር የሆነበት" እየዘመሩ፡ ለሕዝብና ለሀገር እንደጮሁ፡ መሆኑን በመመስከር ታሪካቸው ታሪካችን፡ ደማቸው ደማችን ነውና፡ እነሱን እያስታወስን አኩሪ ተጋድሏችንን ከታሪክ በራዦችና ጥላሸት ቀቢዎች በመጠበቅና በመከላከል ቀጣዩ አዲስ ትውልድ እነማን እንደነበርንና ምን ሠርተን እንዳለፍን ግንዛቤ በማስጨበጥ ከእኛ ሊቀስም ከሚችለው ትምህርት በመውሰድ ሀገሩንና ሕዝቡን አፍቃሪ ብቁ ዜጋ ይሆን ዘንድ ማዘጋጀት ይጠበቅብናል።

የዚያን ትውልድ ታሪክ ማሰባሰብና ለታሪክ ተመራማሪዎች፡ ፀሀፊዎችና ለተተኪው ትውልድ ማስረከብ አንዱ ተልዕኮው አድርጎ የተነሳው የዚያ ትውልድ አካል ሜይ ዴይን በማስታወስ ለሀገራቸው ሉዓላዊነትና ለሕዝባቸው ክብር ሲሉ በተለያዩ አገዛዞች መስዋትነት ለከፈሉና እየከፈሉ ላሉ እንዲሁም በኢሕአፓ ጥላ ሥር ተሰልፈው በትውልድ መመተር ቀይ ሽብርና ነፃ እርምጃ ለወደቁት ወገኖቻችን መታሰቢያ ይሆን ዘንድ የዛሬ ሰባት ዓመት ለሕዝብ ያስተዋወቅነው **ያ ትውልድ ድረ ገጽ** www.yatewlid.org, www.yatewlid.com, ደርግ ለቀበራቸው የያ ትውልድ ወገኖች ሐውልት ሁኖ ዛሬን እዘክራችዋለን።

ለምን ሞቱ? ብትባሉ ለሀገር ባዜማችሁ፣ ለላብ አደሩ በጮሃችሁ፣ ለሕዝባዊ መንግሥት ድምፃችሁን ባሰማችሁ መሆኑን እንመሰክራለን። ገዳይ ግድያውን ሕጋዊ ሽፋን ለመስጠት እንደሚያላዝነው ሀገር ልትገነጥሉ፣ ለባዕድ ቅጥረኞች ሁናችሁ፣ የዓዜው ሥርዓት ናፋቂ ሁናችሁ፣ ሥርዓተ አልበኛ፣ አሸባሪ ሁናችሁ እንዳልሆን ቋሚዎች ለታሪካችሁ ምሥክር በመሆን ትውልድ እንዲያነሳችሁ ጉዟችን ረጅም፣ ግባችንም እሩቅ ነው።

ደርግ በቤት ለቤት አሰሳ፣ አስሦ መደምሰስ፣ በነፃ እርምጃ እና ቀይ ሽብር አንድ ብርቅዬ ትውልድ ጨረሰ። ሀገሪቷ በድህነት አቅሟ ለልማትና ለዕድገት የኮተኮተቻቸው ልጆቿን ደርግ በላ። ለሕዝብ መብትና ነፃነት በግምባር ቀደምትነት የተሰለፉ ጀግኖች ልጆቿን፤ እምቡጥ አበባዎቿን ኢትዮጵያ ተነጠቀች። ኢትዮጵያዊነት ኩራቷን መለያ ክብሯን ጥቁር ድባብ አጠላባት። እምቢኝ ለመብቴ፤ እምቢኝ ለሀገሬ፡ እምቢኝ ለሕዝቤ ያለ ትውልድ በጥይት ተለቀመ። እየታነቁ ተገደሉ። በቁማቸው ከገደል አፋፍ ተወረወሩ። ወደ ባህር ተጣሉ። ሕጻናት ይህን አረመኔያዊ ድርጊት እያዩ እንዲያድጉ ተደረገ። የዚህ አረመኔ አገዛዝ ጦስ ለዛሬም ተርፎ ብሔራዊ ስሜት እተሸረሸረበት፤ ያባት የእናቶቻችን ጀግንነት ተረት እሆነበት ጊዜ ላይ አድርሶናል።

«ያ ትውልድ ተቋም» ለሀገራቸው ክብርና ለሕዝባቸው መብት ሲፋለሙ ክቡር ሕይወታቸውን ለሰዉት የኢትዮጵያ ጀግኖችና የያ ትውልድ ሰማዕታት መታሰቢያነት በያ ትውልድ ስም ያ ትውልድ ድረ ገጽን (www.yatewlid.com www.yatewlid.org ) ለሕዝብ ይፋ ያደረግንበትን ሚያዝያ 23 ቀን 2004 ዓ.ም. ሰባተኛ ዓመት ስናከብር ታሪካችን ከትውልድ ትውልድ ይተላለፍ ዘንድ በሩን ከፍተናልና በታላቅ ደስታ ነው። ዛሬ አጠገባችን የሌሉትን ወንድምና እህቶቻችንን ቢያንስ ስማቸውንና ምስላቸውን እንደያዘ ሚተላለፍ በየትም ሀገርና ቦታ ሆነው የሚያዩት ሐውልት አቁመንላቸዋልና ከተቀበልነው ኑዛዜ ጠብታዋን በማድረጋችን፡ በመጀመራችን እየተደሰትን ከፊታችን የተደቀነውን ከባድ ኃላፊነት በትጋትና በሙሉ ስሜት ለመወጣት ቃል በመግባት ነው።

ተጋድሏችሁንና ታሪካችሁን ለማንኳሰስ፣ ለማንቋሸሽ በ "ቸ" ና "ሸ" የተጣላ ትውልድ፣ እርስ በርሱ የተላለቀ በማለት በሚገባ ያልተፃፈለትን የደርግ ቀይ ሽብር ፍጅት ወደ ጎን ሊገፉ ለሚጥሩና ለሚደሰኩሩ ለማንነታችሁና ለሀገር መስዋዕትነታችሁ ዘብ ቋሚዎች መሆናችንን "ያ ትውልድ ተቋም" አበክረን እንሞግትላችኋለን። ለእኛ መኖር የከፈላችሁትን መስዋዕትነት፣ ዘላችሁ ሳትጠግቡ ያፈሰሳችሁትን ደም ከቶም አንዘነጋውም።

እናንት የሜይ ዴይ ሰማዕታት

ማንነታችሁን ለሀገር የሰጣችሁ፤
ጩኸታችሁን ለሕዝብ ያረጋችሁ፤
ቢወቀጥ አጥንቱ፣ ቢንቆረቆር ደሜ፤
ለሀገር ልምላሜ
ይህ ነበር ቃናችሁ፤
ይህ ነበር ድምጻችሁ
ለጥይት የዳረጋችሁ
ከሀገር የለያችሁ
ለሕይወት ሞት ያበቃችሁ።

ውድ የኢትዮጵያ ልጆችና ሕዝባችን! ከጎናችን ሳትለዩ ላበረታታችሁን የያ ትውልድ ወገኖችና አካላት፤ በተለያየ ወቅት ትብብር ላደረጋችሁልን የሚዲያ፣ የድረ ገጽ ወገኖችና በጠንካራ መሰረት በመሰባሰብ እዚህ ላደረሳችሁት የ«ያ ትውልድ ተቋም» አባላት በሞላ የዓለም ሠራተኞችን ቀን ሜይ ዴይ 2004 ዓ.ም.ን ምክንያት በማድረግ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋ ላደረግነው ያ ትውልድ ድረ ገጽ ሰባተኛ ዓመት ክብረ በዓል እንኳን በደህና አደረሳችሁ እያልን ዝክረ ሜይ ዴይ ሰማዕታት 42ኛ ዓመትን ስናስታውስ ጾታ፣ ዕድሜ፣ ዘር፣ ክልል፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት ሳይለያቸው ለሀገርና ለሕዝብ በአንድነት ተቃቅፈው በየአስፏልቱና ጉራንጉሩ የተዘረገትን፣ የተደፋትን ወገኖቻችንን እያስታወስን ነው።

የቀይ ሽብር ሰማዕታት ወገኖቻችን ደም አይደርቅም!

ዛሬም ስለ ፍትህ እንጮኻለን!

«ያ ትውልድ ተቋም» ለመረጃ ምንጭነት!
የተጐዱ ወገኖችን ለመርዳት!
ለያ ትውልድ መታሰቢያነት!

«ያ ትውልድ ተቋም»


- ስልክ ፡ (703) 300 4302
- ኢሜል ፡ yatewlid@gmail.com,
- ድረ ገጽ ፡ http://www.yatewlid.com, http://www.yatewlid.org, www.redterror.org, www.thatgeneration.org
- ምስለ ገጽ ፡ yatewlid


ሚያዝያ 21 ቀን 2011 ዓ.ም. (May Day 2019)

***ሜይ ዴይ 1969 ዓ.ም.ን አስመልክቶ በየዓመቱ በ "ያ ትውልድ ተቋም" ከወጡ ጽሑፎች***

http://yatewlid.com/images/PDF/YT/YT_Issue/YTT-May-Day-2013.pdf
http://yatewlid.com/images/PDF/YT/YT_Issue/YT_Vol_1/Ya_Tewlid_Vol_1_No_5_Miazia_21_2006.pdf
http://yatewlid.com/images/PDF/YT/YT_Issue/YT_Vol_3/Ya_Tewlid_Vol_3_No_5_Miazia_21_2008.pdf
http://yatewlid.com/images/PDF/YT/YT_Issue/YT_Vol_5/Ya_Tewlid_Vol_5_No_4_MayDay_2010.pdf